# ክልላዊ ትብብር ለኢትዮጵያ የአማራጭ ሳይሆን የግዴታ ሆኗል

**በነብዩ ተድላ** (n_tedla@yahoo.com)

የአፍሪካ ቀንድ በዓለም የጂኦ-ፖለቲካዊ አሰላለፍ ረገድ ከነበረውና አሁን ካለው ከፍተኛ ጠቀሜታ አንፃር ከረዥም ጊዜያት አንስቶ በዓለም ላይ የተፈራረቁ የተለያዩ ርዕዮት አራማጆችና ስትራቴጂስቶች፤ አገራዊና አገራዊ ያልሆኑ የፖለቲካ አድራጊና ፈጣሪዎች ካላቸው የፖለቲካ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ወታደራዊ፣ ሃይማኖታዊና ሌላም ፍላጎት ከመነሳት የተለያዩ State እና Non-State Actors በቀጠናው አዎንታዊና አሉታዊ ጫናቸውን ሲይሳደሩበት የቆየ የአፍሪካ አንድ የትርምስ ጥግ ሆኖ ቆይቷል፡፡

ክፍለ አህጉሩ ከአውሮጠ በስዊዝ ቦይ በኩል ወደ መካከለኛውና ሩቅ ምስራቅ የመተላለፊያ ቁልፍ ኮሪደር በመሆኑና መካከለኛው ምስራቅን ከአፍሪካ ጋር አገናኝ ድልድይ ሆኖ ከማገልገሉ ጋር ተያይዞ የመልካምና የእኩይ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ፣ የንግድ የሃይማኖትና የመሳሰሉት እሳቤዎችና እንቅስቃሴዎች እንዲያስተናግድ አስገድዶታል፡፡ በእነዚሁና በሌሎች ተያያዥ ምክንያቶች የክልሉ ሀገራትና ህዝቦች ገንዘባቸውን፣ አቅማቸውን፣ ጊዜያቸውን፣ ሀብቶቻቸውን አገራቸውን እንደ አገር ጭምር ለእነዚህ ኃይሎች ግብር ያስገቡበትን አስከፊ ሁኔታን ፈጥሮ አልፏል፡፡

በወቅቱ የአካባቢው አገራት ብሔራዊና ክፍለ አህጉራዊ ጥቅም ከጂኦ ስትራቴጂስቶቹ ጥቅም በልጦ ሲገኝ ደም አፋሳሽ የእርስ በርስም ሆነ ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆነ ትርምስ እንዲፈጠር ተደርጎ ተጠቃሚዎቹ በአካባቢው ላይ ልዕለ ኃያልነታቸውንና ጥቅማቸውን ሲያረጋግጡ ቆይተዋል፡፡ ይህ ማለት ደግሞ የአፍሪካ ቀንድ ሀገራትና ህዝቦች ብሔራዊና የጋራ ጥቅሞች ወደጎን ተደርገው ማለት ነው፡፡

በቀጠናው የውጭ ኃይሎች የራሳቸውን ጥቅም ለማስከበርና ለማስጠበቅ ከሚያደርጉት ጣልቃ ገብነት በተጓዳኝ አካባቢው ለዘመናት የልማት፣ የዲሞክራሲና የመልካም አስተዳደር እጦት ውስጣዊ ችግሮችም እኩል እንደመጤዎቹ ሁሉ አካባቢውን ሲንጡት ቆይተዋል፡፡ እነዚህን ስር የሰደዱ ችግሮች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከኢትዮጵያና አጎራባቾቿ ከክልሉ ለመቅረፍ ባለፉት ዓመታት አበረታች እንቅስቃሴዎች እየተደረጉ ይገኛሉ፡፡

የኢትዮጵያ መንግሥት ከአጎራባች አገሮች ጋር ይጠቅሙኛል ብሎ ባሰባቸው መስኮች ሁሉ የትብብር ሥራዎችን በማጠናከር ላይ ይገኛል፡፡ ከእነዚህ የጋራ የትብብር ሥራዎች ውስጥም በጉልህ ስፍራ የሚቀመጠው ለጎረቤት አገሮች የሚደረገው የተፈጥሮ ታዳሽ ኃይል የሽያጭ ሥራና ኢትዮጵያን ከጎረቤት አገሮች ጋር በተለያዩ የመሠረተ ልማት አውታሮች የማስተሳሰር

ሥራ ይገኝበታል። በዋነኛነትም በቅርቡ በኢትዮጵያና ጅቡቲ የተደረገው የኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ ሥራና ከቀናት በፊት በኬንያ፣ ኢትዮጵያና ደቡብ ሱዳን ርዕሳነ ብሔራት ይፋ የሆነው የጋራ የመሠረተ ልማት ትብብር ፕሮጀክቶች በዋናነት ይጠቀሳል።

ኢትዮጵያ ከጅቡቲና ኬንያ ጋር በአፍሪካ ቀንድ ለዘመናት ሰፍኖ በቆየው የመንግስታት የእርስ በርስ  የመጠላለፍ ድራማና ሌሎች ውጥረቶች በአንፃሩ ሠላም የሠፈነበት የሁለትዮሽና የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት የነበራቸው አገራት ሲሆኑ በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በኢኮኖሚው መስክ አመርቂና ተምሳሌታዊ ትስስርን እየፈጠሩ ይገኛል።

ከዚህ አኳያ ኢትዮጵያና ጅቡቲ እንዲሁም የኢትዮ–ኬንያ እና ኢትዮ–ሱዳን ግንኙነት ሲፈተሽ አገራቱ በጋራ የሚሠሩባቸው ኮሚሽኖችና የትብብር መድረኮች ከላይኛው የመንግስት አስተዳደር እስከ ታችኛው የአስተዳደር እርከኖች ጭምር አቋቁመው እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ እነደሚገኙ ሠነዶች ያስነብባሉ። በተለይም በታችኞቹ የአስተዳደር እርከኖች የተፈጠሩ የሁለትዮሽ ትስስሮች በየቀኑ በድንበር አካባቢ እየተከሰቱ ዘላቂ የሠላም የልማትና የአስተዳደር ሥራዎች በአገራቱ መካከል እንዳይሠሩ ማነቆ የሚሆኑ ግጭቶችና ችግሮችን መፍትሄ ከመስጠት አንፃር ውጤታማ እንደሆኑ ፕሮፌሰር ስታንስንስ ማራሮ የተሰኙ በአካባቢው ጥናት ያደረጉ ምሁር አብነታቸውን ይሰጣሉ።

ከዚያ ባሻገር ኢትዮጵያ፣ ጅቡቲና ኬንያ በአካባቢው የሚከሰቱ የሽፍታ፣ የሽብርተኝነትና የአክራሪዎች ስጋቶችን እርስ በርስ በጋራና ከሌሎች አጋሮች ጋር በመሆን አወንታዊ ሥራዎች እያከናወኑ እንደሆነም ይታወቃል።

<u>በጋራ የመልማት ፍላጐት አንድምታ</u>

ኢትዮጵያና ጅቡቲ በሁለትዮሽ የትብብር መስክ ረገድ በዋነኛነት ሊጠቀስ የሚገባው ላለፉት ሁለት ዓመታት ግንባታው ሲካሄድ የቆየውና ከወራቶች በፊት በሁለቱ አገሮች መሪሄ መንግስታት ተመርቆ ወደ ተግባር የተሸጋገረውና በጋራ የመልማት ፍላጐት ተምሳሌት የሆነው የኢትዮ–ጅቡቲ የኃይል ማስተላለፊያና ማስፋፊያ ፕሮጀክት ነው። ፕሮጀክቱ ሁለቱ አገሮች ተለይተው ይታወቁበት ከነበረው የወደብ አጠቃቀም ግንኙነት ባለፈ ለትስስራቸው አዲስ ምዕራፍን ከመክፈቱ በተጨማሪ የሀገራቱን ህዝቦች የጋራ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ የቻለ ክስተት ነው።

ይህ የኃይል ማስተላለፊያና ማስፋፊያ አትዮጵያና ጅቡቲ ያላቸውን የሁለትዮሽ ግንኙነት ከማጠናከር አንድ እርከን ተሻግሮ ለክፍለ አህጉሩና አጠቃላይ ለአፍሪካ የኢኮኖሚ ማህበረሰቦች ትስስር መጎልበት ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ይኖረዋል። ፕሮጀክቱ የጅቡቲን የኃይል ረሀብ

ከማስታገሱ ጐን ለጐን የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ የማሳደግ ብሎም የክፍለ አህጉሩን የኃይል ፍላጐት በታዳሽና ከካርቦን ብክለት ፀድ የሆነ አስተማማኝ የኃይል አቅርቦት ለማረጋገጥ መሠረት የጣለ ጅማሮ በመሆኑ ልማት ወዳድ የሆነውን ሁሉ በእጅጉ አስደስቷል፡፡ እሰየው አስብሏል፡፡

በእርግጥ የዚህን ጽሑፍ አቅራቢ ጨምሮ ብዙዎች ምነው የራሳችንን የኃይል ፍላጐት በቅጡ ሳናረካ ወደ ጎረቤት አገሮች አሳልፎ መሸጥ ምን የሚሉት ፌሊጥ ነው ብለው ጠይቀው እንደነበር ጥርጥር የለውም፡፡ ሆኖም የዚህ ፕሮጀክት አንድምታ ጊዜያዊ የኃይል ፍላጐትን ሙሉ በሙሉ ከማርካት ተሻግሮ የረዥም ጊዜ ጠቀሜታን ያለመ ስትራቴጂያዊ አካሄድ መሆኑን ግን የልብ ይሏል፡፡ መገንዘብም ያስፈልጋል፡፡

በተለይም በኢትዮጵያ ለረዥም ዘመናት አገልግሎት ከሰጡና እየሰጡ ያሉ የኃይል ማስተላለፊያዎች ማርጀትና ኃይል የመሸከም አቅም መዳከምና ሌሎች ችግሮች ጋር ተያይዞ በየጊዜው የመብራት መቋረጥ የሁላችንንም ቤት ማንኳኳቱ አልቀረም፡፡

እነዚህን ያረጁና በቅጡ ያልተሟሉ የኃይል ማስተላለፊያ መስመሮች በተገቢው ሁኔታ በወቅቱ ለመተካትና ለመዘርጋት ግን ቀላል የማይባል ወጪን የሚጠይቅ በመሆኑ ይህንን በተፈለገው ፍጥነትና ጥራት መንግስት ለማከናወን እንዳልቻለ መገመት አያዳግትም፡፡ ሆኖም ከኢትዮ–ጂቡቲ የኃይል ሽይጭ የሚገኘው የውጪ ምንዛሬ (ከ1.3 እስከ 1.5 ሚሊዮን ዶላር ወርሃዊ ገቢ) ይህንና ሌሎች ተመሳሳይ ችግሮችን ለመቅረፍ እንዲሁም አዳዲስ ፕሮጀክቶችን ለማስፋፋትና ወደ ሥራ ለማስገባት የሚውል የውጭ ምንዛሬ እንደሚያመጣ ስንሰማ ቅሬታችንን አንስተናል፡፡

ይህ ገቢ የአገሪቱን የመሠረተ ልማት መስፋፋት ለማረጋገጥ ከፍተኛ እገዛ ከማድረጉም በላይ ኢትዮጵያ አሁን የጀመረችውን የህዳሴውን ግድብና ግልገል ጊቤን የመሰሉ በመስመር ውስጥ ያሉ ቀጣይ ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ እንዲሆኑ የሚያረጋግጥና በአካባቢው አስተማማኝ የኤሌክትሪክ ኃይል በማቅረብ ረገድ ኢትዮጵያን በቁንጮነት የሚያስቀምጥ ይሆናል፡፡

ከዚህ ባለፈም ከምሽቱ 5፡00 ሰዓት እስከ ንጋቱ 11፡00 ሰዓት ድረስ ለጅቡቲ አገልግሎት የሚሰጠው የዚህ የኃይል ማስተላለፊያ ፕሮጀክት ከፍተኛ የሆነ የፖለቲካ አንድምታን ያዘለ፣ ኢትዮጵያን በአፍሪካ ቀንድና በአጠቃላይም በቀጠናውና በአህጉሩ ያላትን ተባብሮ የመልማትና የማደግ ፍላጐትና አቋምን ለሌሎች አገራትና አካላት ማሳወቅ የቻለ እንደሆነ መገንዘብ ያሻል፡፡ በተለይም በአካባቢው ያሉ ሌሎች አገሮች በተመሳሳይ ከኢትዮጵያ ተጠቃሚነታቸውን ማረጋገጥ ከቻሉ በክልሉ በረባም ባልረባም ምክንያት የሚነሱ ቁርሾዎችን ድምጥማጣቸውን

እንደሚያጠፉ መካድ አይቻልም። ጥቅሙ የጋራ ነውና። ኢትዮጵያም ይህን የምታደርገው የተትረፈረፈ ኃይል አጨናንቋት እንዳልሆነ ለመረዳት አይቸግርም። በአሁኑ ወቅት ያለው ብቸኛ አማራጭ ይኸው ትብብር ብቻ መሆኑ እንጂ።

የዚሁ በጋራ የመልማት ፈላጎት አንድምታ ሁለተኛ መገለጫ የሆነው ከቀናት በፊት በኬንያ የባህር ዳርቻ የሚገኘውና ማኅጎኒ በተሰኘው ስፍራ ላይ የኢትዮጵያ፣ ኬንያና በቅርቡ ነፃነቷን የተቀዳጀችው ደቡብ ሱዳን ርዕሳነ ብሔራት አገራቸውን በዘርፈ ብዙ የመሠረተ ልማት አውታር ለማስተሳሰር ስምምነት ላይ የደረሱት የላሙ–ደቡብ ሱዳን–ኢትዮጵያ (LAPSSET) የትራንስፖርት ኮሪደር ፕሮጀክት በዋነኛነት ተጠቃሽ ነው።

ይህ ፕሮጀክት አጠቃላይ ወጪው እስከ 24.5 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር እንደሚፈጅ እየተነገረ ሲሆን ወጭውን ሦስቱ አገራት በጋራ ፋይናንስ እንደሚያደርጉትና በተጨማሪም አህጉራዊና ዓለምአቀፍ የፋይናንስና የልማት ተቋማት እንዲሁም የአገራቱ የልማት አጋሮች ድጋፍ እንደሚያደርጉለት ተዘግቧል።

ይህ የሦስቱ አገራት የጋራ ፕሮጀክት በኬንያ ላሙ ባህር ዳርቻ ላይ ዓለምአቀፍ ደረጃውን የጠበቀ ትልቅ ወደብ፣ ከወደቡ ወደ ደቡብ ሱዳንና ኢትዮጵያ በኬንያዋ ኢሶሎ ከተማ በኩል የሚዘረጉ የባቡርና ደረጃውን የጠበቀ አገር አቋራጭ መንገድና የፋይበር ኦፕቲክስ ግንባታና ዝርጋታዎች ይኖራሉ። በተጨማሪም የነዳጅ ማጣሪያ፣ የነዳጅ ማስተላለፊያ መስመሮች ዝርጋታ፣ ሦስት አየር ማረፊያዎችና የቱሪስት መስህብ የሚሆኑ የመዝናኛ ሥፍራዎችን ፕሮጀክቱ ያካትታል። ኬንያ የላሙ ወደብ ሲጠናቀቅም ኢትዮጵያ የራሷን ዕቃ የምታራግፍበትና የምታከማችበት ወደቡ ላይ የሚገኝ 20 ሄክታር መሬት ለኢትዮጵያ መስጠቷን መረጃዎች ያመላክታሉ።

ይህ ፕሮጀክት በሦስቱ አገሮች እስካሁን የነበረውን የተቀዛቀዘ የንግድ እንቅስቃሴ የሚያሟሙቅና ከሚገነቡት የኢኮኖሚና የመሠረተ ልማቶች አንፃር ሰፊ የንግድ ቀጠናን እንደሚፈጥርላቸው ይታመናል። በዚሁም የአገራቱ የእርስ በርስ ድንበር ተሻጋሪ ንግድ ይጠናከራል፣ የትራንስፖርትና የትራንዚት ወጪና ጊዜን ይቀንሳል። አጠቃላይ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማትን በክልሉ እንደሚያፋጥንም ይጠበቃል። ከዚሁ ፕሮጀክት አገራቱ የ2.3 በመቶ የGDP ዕድገት እንደሚያስመዘግቡ የዓለም ባንክን ጨምሮ አንዳንድ ተቋማት ከወዲሁ መተንበይ ይዘዋል። ፕሮጀክቱ የሚዘረጋባቸውና ከዚህ ቀደም በየአገራቱ በርቀት ምክንያት ለተመሳሳይ የኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ተገድበው የነበሩ አካባቢዎች አሁን ምቹ ሁኔታ ይፈጠርላቸዋል። በአጠቃላይም ወደ 167 ሚሊዮን የሚጠጉ የክልሉ ነዋሪዎች ከፕሮጀክቱ ከሚፈጠሩ ዕድሎች ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ይጠቀሳል። ይህ ዕድል ለሦስቱ አገራት ብሎም

ለክፍለ አህጉሩ አገራትና ህዝቦች የጋራ የትብብር ሁኔታን የሚፈጥርና የሀገራቱን ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት በጋራ ተጠቃሚነት ዕይታ የሚያጠናክር እንደሚሆንም ጥርጥር የለውም፡፡

ከዚህ አኳያ ፕሮጀክቱ ክልሉን ቀፍድዶ ይዞ ከነበረው የሎጂስቲክስና መሠረተ ልማት አቅርቦት ችግር ቀስ በቀስ የሚፈታ መሆኑ ለኢትዮጵያም ትልቅ አንድምታ ይኖረዋል፡፡ ኢትዮጵያ ላለፉት ዓመታት ተስፋ ሰጪ የኢኮኖሚ ዕድገት ማስመዝገቧና የወጪና የገቢ ምርቶቿ እየበዙ መምጣቱ ካለምንም ጥርጥር ተጨማሪና አስተማማኝ ወደብ እያስፈለጋት መሄዱ አይቀሬ ነው፡፡ በተለይም መንግሥት በቀጣይ ዓመታት ወደ ኢንዱስትሪ ልማት ለመሸጋገር ያስቀመጠውን ዕቅድ ከማረጋገጥ አኳያ፡፡

እንደ ጅቡቲው ሁሉ ኢትዮጵያ ከሱዳን ጋር በኃይል ማስተላለፊያ ለመተሳሰር የመስመር ግንባታው በቅርቡ መጠናቀቁን የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክና ኃይል ኮርፖሬሽን ይፋ ማድረጉ ይታወሳል፡፡ ይህ የዓለም ባንክ ፋይናንስ ያደረገውና 41 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር የወጣበት ፕሮጀክት ወደ ሱዳን በቅድሚያ 100 ሜጋ ዋት መሸጥ የሚያስችል ይሆናል፡፡ እንደ ዓለም ባንክ ሪፖርቶች ገለፃም ሱዳን አካባቢ በካይ ሆኖ ከቆየውና ኤሌክትሪክ ለማመንጨት ስትጠቀምበት ከነበረው የሙቀት ኃይል ማመንጫ (Thermal Energy) ያላቅቃታል፡፡ በተመሳሳይ ኢትዮጵያ ለኬንያ በዓመት ከ400 እስከ 600 ሜጋ ዋት የሚደርስ ኃይል ለመሸጥ በሁለቱ አገራት መካከል ስምምነት ላይ መደረሱ በክልሉ እያደገ የመጣውን ትብብርና የእርስ በርስ መተማመን መጨመር ያሳያል፡፡ አፍሪካ በአሁኑ ወቅት ፈጣን የኢኮኖሚ ልማት በማስመዝገብ ላይ ያሉ በርካታ አገሮችን አካታ ይዛለች፡፡ እነዚህ አገሮች ደግሞ የተያያዙትን የልማት እንቅስቃሴ የሚመግብ አስተማማኝ የኃይል አቅርቦት ያስፈልጋል፡፡ የኢትዮ–ኬንያ፣ የኢትዮ–ሱዳንና የኢትዮ–ጅቡቲም በዚሁ የትብብር ማዕቀፍ የሚታይ ይሆናል፡፡

## የፕሮጀክቱ ፈተናዎች

የላሙ–ደቡብ ሱዳን–ኢትዮጵያ የመሠረተ ልማት ማስፋፊያ ፕሮጀክት ይፋ ከሆነበት ደቂቃ አንስቶ በፕሮጀክቱ ላይ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ሂስ ያቀረቡና ፕሮጀክቱ ሊያጋጥመው የሚችሉ ፈተናዎችን የጠቃቀሱ በርካታ አካላት መኖራቸውን መገንዘብ የግድ ይሏል፡፡ ሆኖም እነዚህ አካላት ሀሳብ ስላቀረቡ ብቻ ሳይሆን ለክልሉ አገራትና ህዝቦች ዘላቂ ጥቅም ሲባል ከፕሮጀክቱ ጋር ተያይዘው ሊከሰቱ የሚችሉ ፈተናዎችን ከወዲሁ ተንብዮ ምላሽ እየሰጡ ማለፍ ተገቢ ይሆናል፡፡

የላሙ ወደብ የሚገነባበት የላሙ የባህር ዳርቻና አካባቢው ለረዥም ጊዜ በኬንያ የነበሩ መንግስታት ተረስቶ የቆየና ልማት የራቀው አባባቢ ነው ብለው የአካባቢው የላሙ ተወላጆች ያምናሉ፡፡ ፕሮጀክቱ ወደፊትም ቢሆን ለላሙ ህዝብ የሚፈይደው ጉዳይ አይኖርም ብለው የሚከራከሩ ወገኖች አልጠፉም፡፡ እርግጥ የኬንያ መንግስት ከፕሮጀክቱ ይፋ መሆን ጋር ተያይዞ 1 ሺህ የሚሆኑ የላሙ ወጣቶች ሥልጠና አግኝተው በዚሁ የመሠረተ ልማት ማስፋፊያ እንቅስቃሴ ውስጥ የሥራ ዕድል እንዲያገኙ ውሳኔ አስተላልፏል፡፡ በሌላ በኩል የላሙ ወደብ፣ የባቡርና የመንገድ ግንባታዎች እንዲሁም የነዳጅ ማጣሪያና ማስተላለፊያ መስመሮች በአካባቢው ሲገነቡ የአካባቢውን ደን የሚመነጥርና በዩኔስኮ በዓለም ቅርስነት የተመዘገበውን በአካባቢው የሚገኝ የስዋህሊ አፍሪካውያን እስልምና ተከታዮች ጥንታዊ የህንፃ ግንባታ ጥበብ የያዙ ቅርሶችን አደጋ ላይ እንደሚጥል ተጠቅሷል፡፡

ቀደም ሲል ከተጠቀሰው ጋር አያይዞ ፕሮጀክቱ በላሙ የባህር ዳርቻ ባሉ የባህር ህይወትና ስነምህዳር ላይ አደጋ ከማድረሱ በላይ የአካባቢውን ተወላጆች ከመሬታቸው ያፈናቅላል የሚል ክርክርም Save Lamu ከተሰኘ የአካባቢው ተቆርቋሪ ቡድን ነኝ ከሚል አካል ጠንከር ያሉ ወቀሳዎች መቅረብ ጀምረዋል፡፡ ይህ ጉዳይ በቅርብ ታይቶና ከአካባቢው ተወላጆች ጋር በጠ ቀሜታና ጥቅማቸውን በማይጎዳ መልኩ እንዲከናወን በማረጋገጥ ስምምነት ላይ መድረስ የግድ ይላል፡፡

ከወራት በፊት ለላሙ የባህር ዳርቻ ቅርብ ከሆነው የኬንያ የመዝናኛ ሥፍራ በሶማሊያው አሸባሪ ቡድን አልሸባብ የተጠለፉትን ፈረንሳዊት ቱሪስት መሞት ተከትሎ ኬንያ ወደ ሶማሊያ ጦሯን ማስገባቷ ይታወሳል፡፡ የላሙ ወደብና ሌሎች ከኢትዮጵያና ደቡብ ሱዳን ጋር የሚተሳሰሩ መሠረተ ልማቶች እውን መሆን የሶማሊያ መረጋጋት ወሳኝነት ይኖረዋል፡፡ በአካባቢው የሚገኘው የህንድ ውቅያኖስም ዓለምን በዓመት እስከ 7 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር የሚያከስሯት የሶማሊያ የባህር ላይ ወንበዴዎች መፈንጫ እስከሆነ ድረስ የላሙ ወደብ ለባህር ትራንስፖርት ቀይ ሊበራበት ይችላል፡፡ የነዳጅ ማስተላለፊያ መስመሮች፣ አገር አቋራጭ መንገዶችና የባቡር መስመሮችም እንዲሁ፡፡ በአካባቢው በተለይም በሰሜን ኬንያ የሚንቀሳቀሱ ወንበዴዎችና የሽምቅ ተዋጊዎች ጉዳይም በዚሁ አይን ይታያል፡፡

## <u>አዋጪ የደህንነት ማረጋገጫ</u>

የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይና አገራዊ ደህንነት የፖሊሲ ሰነድ በግልፅ እንደሚያስቀምጠው የአገሪቱ የውጭ ግንኙነት ቅድሚያ ትኩረት የሚሰጣቸው የጎረቤት አገሮችና የአፍሪካ ቀንድ ክልልና ጉዳይ ነው፡፡ የአገሪቱን ሰላምና የልማት እንቅስቃሴ በቀጥታና በተዘዋዋሪ መንገድ በከፍተኛ ደረጃ ሊነካ የሚችለው ይህ አካባቢ በመሆኑ የአፍሪካ ቀንድ መልማትና መደህየት ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ልማት በጐም ሆነ አሉታዊ በሆነ መልኩ ቀጥተኛ ተፅዕኖ ማሳደር

ይችላል። የአፍሪካ ቀንድ በኢትዮጵያ መልማትም ከኢትዮጵያ ሕዝብ ቀጥሎ ተጠቃሚ የሚሆን አካባቢ ይሆናል። የኢትዮ–ጂቡቲ፣ የኢትዮ–ኬንያና የኢትዮ–ሱዳን የኃይል ማስተላለፊያና አዲሱ የLAPSSET ፕሮጀክትም በዚሁ መነፅር መታየት የሚገባው ጉዳይ ይሆናል።

ኢትዮጵያ ከሁሉም ጎረቤቶቿ ጋር በሰላም፣ በጋራ ጥቅምና በእኩልነት ላይ የተመሠረተ ግንኙነትን መፍጠር መቻል ይኖርባታል። ቀደም ሲል ከጎረቤት አገሮች በኩል የነበሩና በኢትዮጵያ ላይ ይንፀባረቁ የነበሩ ጥርጣሬዎች አገሪቱ በልማቱ ጎዳና እየገሰገሰች ስትሄድ ተመልሰው ሊያገረሹ ይችላሉና እንዲህ ዓይነቶች ስጋቶችና ጥርጣሬዎች አካባቢያዊ ትስስር ላይ ደንቃራ ከመሆን አልፈው የኢትዮጵያ ሉአላዊነትና ብሔራዊ ጥቅሞች እንዳይከበሩ ሊያደርጉ ይችላሉ።

እንዲህ ዓይነት ጥርጣሬዎችን ግን በኢትዮ–ጂቡቲ የኃይል ማስተላለፊያና በLAPSSET ፕሮጀክት ዓይነት የጋራ ተጠቃሚነትን በሚያረጋግጡ የጋራ ፕሮጀክቶች ጉም ሆነው እንዲበተኑ በማድረግ የኢትዮጵያን ብሎም የአካባቢውን ዘላቂ ልማት ማረጋገጥ ይቻላልና እርምጃው በእጅጉ የሚያስመሰግን ነው። እነዚህን መሰል ፕሮጀክቶች ከጊዜያዊና መለስተኛ ጥቅሞች በላይ ዘልቀው የሚሄዱና ስትራቴጂክ ጠቀሜታን የሚያረጋግጡ ይሆናሉ። በፖለቲካ አኮኖሚ የበላይነት እልህ ከመጋባት ይልቅ ተባብሮ አብሮ በመስራት የኢትዮጵያን ህልውና ማረጋገጥ ይቻላልና። ጐረቤት አገሮች ከታመሱና ከደኸዩ ኢትዮጵያም አይቀርላትም። በዚህ ዓይነት ትብብር ግን ጤናማና ሰላማዊ ግንኙነትን ከማረጋገጥ አልፎ አካባቢውን የሚያምሱ የጥፋት አጀንዳዎችን ነጥሎ ማውጣት እንደሚቻል ጥርጥር የለውም። ጂቡቲ፣ ኬንያ ወይም ሱዳን ከኢትዮጵያ የኃይል ልማት ተጠቃሚ መሆናቸው የኢትዮጵያን ልማት ወዳጅና ቋሚ ጠበቃ እንዲሆኑ ያደርጋል። ይህ ደግሞ ጥቅሙ ለአገሪቱ ብቻ ሳይሆን በተዘዋዋሪ መልሶ ለኢትዮጵያም ስለሚሆን የውሳኔው ብስለት ይደነቃል። ከዚያም አልፎ ኢትዮጵያ በቂና አስተማማኝ የወደብ አገልግሎት በተመጣጣኝ ዋጋ ከጅቡቲ ወይም ከኬንያ ማግኘቷን የሚረጋገጥ ይሆናል።

ይህ የኃይል ሽያጭ ግንኙነትና ሌሎች የመሠረተ ልማት ግንባታዎች ደረጃ በደረጃ ነፃ የንግድ ቀጠና በመፈጠር ለአገራችን ጭምር ተጨማሪ ገበያ መፍጠር መቻል ይኖርባቸዋል። እንደሚፈጥርም ይታመናል። ይህ ሲረጋገጥ ሰፊ ወጪ እያወጡ ግዙፍ የመከላከያ ኃይል በመገንባትና በማቆም ከጎረቤት አገሮች ሊቃጣ የሚችል አደጋን ከመጠባበቅ ይልቅ ጎረቤት አገሮች አንዱ ከሌላው ከሚያገኘው ጥቅም ለራሱ የሚያገኘውን ጥቅም ለመጠበቅ ሲል አንዱ ሌላውን ከአደጋ የሚጠብቅበትን ሁኔታ ማረጋገጡ አዋጪ የደህንነት አካሄድ እንደሆነ አይካድም።

ከዚህ በመነሳት ከጂቡቲ፣ ኬንያና ሁለቱ ሱዳኖች ጋር በቀጣይ በተለይም በወደብ አጠቃቀም፣ በድንበር ጉዳዮች፣ በአየር ትራንስፖርት አገልግሎት፣ በድንበር ዘለል ንግዶች፣ በስደተኞች ጉዳይ፣ በረሀማነትና ድርቅ ጋር እንዲሁም አገራቱ ድንበሮች ላይ ከሚኖሩ ሕዝቦችና ሌሎች ጉዳዮች ጋር ተያይዘው በየጊዜው የሚያጋጥሙ ልዩነቶችን በሰጥቶ መቀበል መርህ በማስተናገድ አንፃራዊ ሰላምና ተጠቃሚነትን እያጠናከሩ መሄድ የግድ ነው። በተለይም ኢትዮጵያ በአሁኑ ሰዓት ካላት ግዙፍ የወጪና የገቢ የማሪታይም እንቅስቃሴ አንፃር ከጅቡቲ፣ ታጁራና ላሙ ወደቦች ባሻገርም ሌሎች ወደቦችን በአማራጭነት ማፈላለግ አንዱን ትቶ ወደሌላው የመሄድ ጉዳይ ሳይሆን በሁሉም ገበቢ ውድድር ሰፍኖ ተጠቃሚነት የማረጋገጥ ጉዳይ እንደሆነ ሁሉም ጎረቤት አገሮች ሊረዱ ያስፈልጋቸዋል። በዚህ ጉዳይ የአገራችን ዲፕሎማቶች ድርሻ የአንበሳውን ድርሻ ይወስዳል።

የኢትዮ–ጅቡቲ የኃይል ማስተላለፊያ ፕሮጀክት ወጪ ሁለቱ አገሮች በጋራ ተካፍለው የሠሩት ሲሆን (ኢትዮጵያ 850 ሚሊዮን ጅቡቲ ደግሞ 650 ሚሊዮን ብር) ጅቡቲ ከሚያስፈልጋት የኃይል አቅም 60 በመቶውን እንደሚሸፍን ተገልጿል። በመስኩ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያሳዩት የጅቡቲ የኃይል ፍላጐት አሁን ከአለበት 90 ሜጋዋት ወደ 175 ሜጋዋት በቀጣዮቹ 15 ዓመታት ውስጥ እንደሚያድግ ይተነብያሉ። በመሆኑም ይህን መሰል ፕሮጀክት ሁለቱ አገሮች አንዱ የአንዱን ክፍተት እንዲሞላ ይረዳል። ኢትዮጵያ የለም መሬትና በአንፃራዊ እይታ የውሃ እጥረት የሌለባት አገር ነች። ጅቡቲ በበኩሏ ባብኤል መንደብን የሚያዋስን የረዥምና አመቺ የወደብ ባለቤት ነች። በቅርቡ ጅቡቲያውያን በስንዴና አበባ እርሻዎች ለመሠማራት በኦሮሚያ አካባቢ መሬት መረከባቸው ይታወሳል። አሁን ደግሞ የኤሌክትሪክ ግዥ ጀምረዋል። ከጅቡቲ በኩል ደግሞ ከወደብ ታሪፍና አገልግሎት ክፍያ ጋር ተያይዞ የወደብ አገልግሎት ክፍያ ተመጣጣኝ እንዲሆን ብሎም ለኢትዮጵያ የልዩ ደንበኛነት የወደብ አገልግሎት ጅቡቲያውያን እንዲሰጡ ሁኔታዎችን እንደሚያመቻች ይጠበቃል። የሁለቱ አገሮች ይህ ጅምር ለቀጣይ የክፍለ አህጉሩ የኢኮኖሚ ትስስር መሠረት የጣለና ወደ ላቀ ደረጃ የሚያሸጋግር ሆኗል። በተመሳሳይ አዲስ ስምምነት የተደረሰበት የላሙ–ደቡብ ሱዳን–ኢትዮጵያ ፕሮጀክትም እንዲሁ ከሚያስፋፋው ሰፊና እርስ በርሱ የተሳሰረ የመሠረተ ልማት ግንባታ አንፃር የክልሉን ውህደት ያፋጥነዋል። ወደፊት አገራቱ የጋራ የመገበያያ ገንዘብና የፖለቲካ ኮንፌዴሬሽን እስከመመስረት ድረስ ማለት ነው።

እነዚህ ፕሮጀክቶች ተመንድገው የአፍሪካ ቀንድና የኢጋድ አገራት ከደቡባዊ አፍሪካ የልማት ማህበረሰብ ሳዴክ እና ከምዕራብ አፍሪካ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ኤኮዋስ ጋር በመሠረተ ልማት እንዲዋሀዱ መመኘት ደግሞ ክፋት ያለው አይመስልም። የአፍሪካ ህብረትና የኔጠድ አላማስ ይኸው አይደል።

## አረንጓዴ ዕድገት ብቸኛው ምርጫ

የኢትዮ–ጂቡቲ የኃይል ማስተላለፊያ ፕሮጀክት ተጠናቆ መመረቁ በቀጣይ ኢትዮጵያ ለኬንያና ሱዳን የታዳሽ ኃይል ለማቅረብ ሁኔታዎች በመጠናቀቅ ላይ መሆናቸው አስተማማኝ የኃይል አቅርቦት ጉዳይ የዓለማችን ቁጥር አንድ አጀንዳ እየሆነ በመጣበት በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያን የታዳሽና ንፁህ ኃይል የማቅረብ አቅም ያሳየና የዚህ ተጠቃሚም ኢትዮጵያ ብቻ ሳትሆን ጎረቤት አገሮች ጭምር እንደሆነ ያረጋገጠ ነው፡፡

በቀጣይ 30 ዓመታተ የዓለም ሕዝብ አሁን ከአለበት 7 ቢሊዮን ወደ 9 ቢሊዮን እንደሚያድግና ቀጣይ የልማት ሥራዎች ያለበቂ ንፁህ የታዳሽ ኃይል ምንጮች ቀጣይነታቸውን ማረጋገጥ የማይቻልበት ደረጃ ላይ እንደሚደርስ እየተተነበየ ይገኛል፡፡ አረንጓዴ ዕድገት ምርጫ ሳይሆን ግዴታ እየሆነ መምጣቱ ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ ነዳጅን የመሰሉ የካርቦን ነክ የኃይል ምንጮች ከጊዜ ወደ ጊዜ የአቅርቦት አስተማማኝነታቸውና ተቀባይነታቸው ጥያቄ ላይ እየገባና ዋጋቸው በየጊዜው እየጨመረ ከመሄዱ አንፃር ኢትዮጵያ የታዳሽ ኃይልን በተመጣጣኝ ዋጋ ማቅረብ መጀመሯ ቀጣዩ ጊዜ ለአገሪቱና ለአጋሮቿ ብሩህ መሆኑን ጭምር አመላክቷል፡፡ ከሁሉ በላይ ደግሞ ከባቢያዊ አየርን የማይበክልና ንፁህ አረንጓዴ የኃይል ምንጭ መሆኑ የአገሪቱ የልማት አቅጣጫ አረንጓዴ እየሆነ መምጣቱን አረጋግጧል፡፡ ይህ ደግሞ የኢትዮጵያ ልማት በዓለም አቀፍ መድረኮች በበጎ ገፅታ እንዲታወቅና ተጨማሪ የልማት እገዛን እንዲያገኝ ያስችለዋል፡፡ ቀድመው የተጀመሩ ፕሮጀክቶች እገዛዎች በብድርና እርዳታ መልክ ለተመሳሳይ ፕሮጀክቶች የሚመጡ ድጋፎች ለታሰበላቸው ዓላማ ሙሉ በሙሉ መዋል እንደሚችሉ ተአማኒነትና ተቀባይነትን በኢትዮጵያ አጎናፅፏል፡፡ ለቀጣዩ የላሙ–ደቡብ ሱዳን–ኢትዮጵያ ፕሮጀክትም መሳካት መሠረት ይጥላል፡፡

ከዚሁ ጎን ለጎን በዓለም አቀፍ ደረጃ ካርቦን ፀድ የሆነ ልማት ወደፊት አጠናክሮ ለመቀጠል የተጀመረውን ዓለም አቀፍ እንቅስቃሴ ኢትዮጵያና የጎረቤት አገሮች ከወዲሁ መቀላቀል መጀመራቸውን ያሳያልና ያስደስታል፡፡ ወደፊትም በብዝሀ–ህይወት መቃወስ ምክንያት በአገራቱ የግብርና ምርታማነት ላይ የሚደርሱትን አሉታዊ ተፅዕኖዎችን ከወዲሁ ለመቅረፍ እንቅስቃሴ መጀመሩን ያረጋግጣል፡፡ በቅርቡ ኖርዌይ ኦስሎ ከተማ በተካሄደው የዓለም አቀፍ የአረንጓዴ ልማት ኮንፈረንስ ላይም ቢሆን የተረጋገጠው ይህ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ከብክለት የፀዳ ቀጣይነት ባለው የታዳሽ ኃይል ላይ የተመሠረተ ፈጣን የኢኮኖሚ ልማት ማካሄድ መጀመሯ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ሊቀመንበር ባንኪሙንና በጉባኤተኞቹ ጭምር በኮንፈረንሱ ላይ በምሳሌነት ቀርቦ ትልቅ አድናቆትን አትርፏል፡፡ ብራቮ ኢትዮጵያ!!!

እነዚህ የጋራ ተጠቃሚነትን የሚያጎለብቱ ፕሮጀክቶች ለአገራቱና ለእኛ ለህዝቦቻቸው ኑሮ መሻሻል መሠረት በመሆናቸው መንግስታቱ እነዚህን የትብብር ማዕቀፎች አጠናክረው እንዲቀጥሉ በሉ እንላለን፡፡ ያለን አማራጭ አብሮ መዋኘት ወይም አብሮ መስጠም ነውና፡፡ ሠላም፡፡